በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
ገንዘብ ሚኒስቴር
The Federal Democratic Republic of Ethiopia
Ministry of Finance

ቁጥር
Ref.No ገ/ኢ/1/2/53
ቀን
Date [illegible]/3/2013

ለገቢዎች ሚኒስቴር
ለጉምሩክ ኮሚሽን
ለኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ
ለንግድና ኢንዱስትሪ ሚኒስቴር
ለግብርና ሚኒስቴር
ለኢትዮጵያ ኢንቨስትመንት ኮሚሽን
<u>አዲስ አበባ</u>

በተፈጥሮና ሰው ሠራሽ አደጋ ምክንያት ንብረታቸው ለወደመባቸው ባለሀብቶች ድጋፍ ስለሚደረግበት ሁኔታ የሚኒስትሮች ምክር ቤት መስከረም 6 ቀን 2013 ዓ.ም ባካሄደው 89ኛ መደበኛ ስብሰባ ውሳኔ ያስተላለፈ መሆኑን ጠቅሰን በምክር ቤቱ ውሳኔ መሠረት በመ/ቤታችን የተዘጋጀውን የአሠራር መመሪያ ቁጥር 69/2013 ለአፈፃፀም እንዲረዳ በ23/2/2013 በቁጥር ገ/ኢ/1/2/49 በተፃፈ ደብዳቤ መላካችንን ይታወሳል፡፡

የመመሪያውን አንቀጽ 9 አፈፃፀም ግልፅ ለማድረግ መመሪያውን ማሻሻል አስፈላጊ ሆኖ ተገኝቷል፡፡

ስለዚህ የተሻሻለውን መመሪያ ለአፈፃፀም እንዲረዳ ከዚህ ጋር አባሪ አድርገን መላካችንን እንገልፃለን፡፡

ከሠላምታ ጋር

አህመድ ሺዴ
ሚኒስትር

ግልባጭ፣
- ለክቡር ሚኒስትር ጽ/ቤት
- ለክቡር የፊሲካል ፖሊሲና ፐብሊክ ፋይናንስ ዘርፍ ሚኒስትር ዴኤታ
- ለሕግ ጉዳዮች ዳይሬክቶሬት
- <u>ገንዘብ ሚኒስቴር</u>

Letter Hab/GT

ስልክ
Tel 251- 11- 155 24 00,22 66 98
251- 11- 155 00 81,83 86 89
የፖ.ሣ.ቁ
P.O.Box 1905,1037
እባክዎን መልስ ሲፅፉልን የኛን ቁጥር ይጥቀሱ
ፋክስ
Fax 251-11-156 01 24,55 14 96
251-11-155 11 38
አዲስ አበባ ኢትዮጵያ
Addis Ababa-Ethiopia

# የገንዘብ ሚኒስቴር

## በተፈጥሮና ሰው ሠራሽ አደጋ ምክንያት ንብረታቸው ለወደመባቸው ባለሀብቶች ድጋፍ ስለሚደረግበት ሁኔታ የወጣን መመሪያ ለማሻሻል የወጣ መመሪያ

ገንዘብ ሚኒስቴር

2013 ዓ.ም

Property Destroyed(1) H/GT

## በተፈጥሮና ሰው ሠራሽ አደጋ ምክንያት ንብረታቸው ለወደመባቸው ባለሀብቶች ድጋፍ ስለሚደረግበት ሁኔታ የወጣን መመሪያ ለማሻሻል የወጣ መመሪያ

1. **አውጪው ባለሥልጣን**

የገንዘብ ሚኒስቴር የሚኒስትሮች ምክር ቤት መስከረም 6 ቀን 2013 ዓ.ም. ባካሄደው 89ኛ መደበኛ ስብሰባ በሰጠው ውክልና መሠረት ከዚህ የሚከተለውን መመሪያ አውጥቷል፡፡

2. **አጭር ርዕስ**

ይህ መመሪያ "በተፈጥሮና ሰው ሠራሽ አደጋ ምክንያት ንብረታቸው ለወደመባቸው ባለሀብቶች በመንግሥት ስለሚደረግ ድጋፍ የወጣው መመሪያ ቁጥር 69/2013 ማሻሻያ መመሪያ" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

3. **ማሻሻያ**

በተፈጥሮና ሰው ሠራሽ አደጋ ምክንያት ንብረታቸው ለወደመባቸው ባለሀብቶች በመንግሥት ስለሚደረግ ድጋፍ የወጣው መመሪያ ቁጥር 69/2013 እንደሚከተለው ተሻሽሏል፡፡

የመመሪያው አንቀጽ (9) ተሠርዞ በሚከተለው አዲስ አንቀጽ (9) ተተክቷል፡፡

"**የአገር ውስጥ ብድር**

በተፈጥሮ ወይም በሰው ሠራሽ አደጋ ምክንያት ንብረታቸው ላይ ጉዳት የደረሰባቸው ባለሀብቶች ንብረታቸውን ለመተካት የሚያስችል ብድር የሚያገኙበት ሁኔታ ወይም ለኢንቨስትመንቱ የወሰዱት ብድር የሚሸጋሸግበት መንገድ በኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ ማቋቋሚያ አዋጅ ቁጥር 591/2000 (እንደተሻሻለ) አንቀጽ 15 ንዑስ አንቀጽ (1)(ሀ)(2) መሠረት ባንኩ በሚያወጣው መመሪያ ተፈፃሚ ይሆናል"

4. **መመሪያው የሚፀናበት ጊዜ**

ይህ መመሪያ ከህዳር 11 ቀን 2013 ዓ.ም. ጀምሮ የፀና ይሆናል፡፡

*አዲስ አበባ ህዳር 10 ቀን 2013 ዓ.ም.*

*አህመድ ሺዴ*
*የገንዘብ ሚኒስትር*

Property Destroyed(1) H/GT